Public Health
Seattle & King County

# በመታጠቢያ ገንዳ ላይ ጥርስን መቦረሽ

*ተቋማት ሁሉ ለየት የሚያደርግ የራሳቸው የሆነ ነገር አላቸው ስለዚህም ከዚህ በታች ያሉት መመሪያዎች በሚያስፈልግበት ጊዜ ሊቀያየሩ ይችላሉ።*

## *ዝግጅት*

- እያንዳንዱ ልጅ **በእጀታው ላይ ስማቸው በግልጽ የተለጠፈበት የራሳቸው** የጥርስ ብሩሽ አላቸው። ማጋራትም ሆነ መበደር አይፈቀድም።
- **በክፍል ውስጥ የእጅ መታጠቢያ ገንዳ** ይጠቀሙ (መታጠቢያ ቤት ውስጥ ያለውን ገንዳ ሳይሆን)። የቧንቧ እና የውሃ ማጠቢያ ገንዳውን በደንብ ይጠቡና የፀረ-ተባይ ማጽጃን ተጠቅመው ያጽዱ።
- ተቋማቱ የሚያቀርበው እንቅስቃሴዎች ላይ የሚሳተፉ ልጆች እና አስተማሪዎች ጥርስ **ከመቦረሻቸው በፊት እጃቸውን ይታጠቡ**። በተጨማሪም መምህራን የሚጣሉ ጓንቶችን ሊለብሱ ይችላሉ።
- የውሀ ማንቆርቆሪያውን ከንፁህ ውሃ ምንጭ በሚመጣ ንጹህ ውሀ (ለምሳሌ ከምግብ ማቅረቢያ ማጠቢያ ወይም የውሃ ማከፋፈያ ገንዳ) ይሙሉ።
- ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው የሚሸጋገሩ ብክለቶችን ለመቀነስ **መምህሩ በኩባያ ወይም በሳህን ጠርዝ ዙሪያ ላይ ፍሎራይድ ያለውን የጥርስ ሳሙና** (በሥዕሉ ላይ እንደሚታየው አድርጎ) **በትንንሹ ጠብ አድርጎ ያስቀምጥ**።
    - ዕድሜያቸው ከ 3 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች ሩዝን የሚያክል ጠብታ
    - ዕድሜያቸው ከ3-6 ዓመት ለሆኑ ልጆች አንድ አተርን የሚያክል ጠብታ




***የጥርስ ብሩሾችን በየ 3-4 ወሩ ይቀይሩ ወይም ከሌላ ልጅ የጥርስ ብሩሽ ጋር ወይም ንፁህ ካልሆነ ቦታ ጋር ከተገናኙ ወይም በሌላ ልጅ ጥቅም ላይ ከዋሉ ወይም ብሩሾቹ ከተሰባበሩ ወይም ካረጁ ከዚያ ቀደም ብለው ይቀይሩ።***

## *ጥርስ በሚቦርሹበት ጊዜ የልጆችን ድርጊት ይቆጣጠሩ*

- መምህሩ የልጁን የጥርስ ብሩሽ ከመደርደሪያው ላይ ወስዶ፣ ቀደም ብሎ የወጣውን አንድ ነጥብ የጥርስ ሳሙና በብሩሽ ላይ አስቀምጦ፣ ለልጁ የጥርስ ብሩሹን እና ትንሽ ንጹህ ውሃ የያዘ የወረቀት ኩባያ ይሰጠዋል።
- ልጁ በሚነክሰው ቦታ ላይ፣ ከዚያም በአፍ ዙሪያ ከግራ ወደ ቀኝ እና ከላይ ወደ ታች መቦረሽ ይጀምራል። **መቦረሹን ለ2 ደቂቃዎች ይቀጥላል።** (በደንብ በአጥጋቢ ሁኔታ በማይቦርሹበትም ጊዜ ፍሎራይዳድ ያለውን የጥርስ ሳሙናን መጠቀም ጠቃሚ ነው።)
- ልጁ ከኩባያው ውስጥ ትንሽ ውሃ ወስዶ አፉ ውስጥ ውሃውን ተጉሞጥሙጦ ውሃውን እና የተረፈውን የጥርስ ሳሙና ወደ ማጠቢያ ገንዳው ወይም ኩባያው ውስጥ ይተፋል።
- ልጁ በመታጠቢያ ገንዳው ላይ የጥርስ ብሩሹን ይይዝና መምህሩ ከውሃ ማንቆርቆሪያው ውስጥ ያለውን ንፁህ ውሃ ብሩሹ ላይ ያፈሳል። ***(የጥርሱን ብሩሽ ከእጅ መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ በሚወጣ ውሃ ተጠቅመው በጭራሽ እንዳያጥቡ።)***




## *ፅዳት*

- ልጁ የጥርስ ብሩሹን ለአስተማሪው ይሰጣል፣ አስተማሪውም የጥርስ ብሩሹን ለልጁ በተዘጋጀው ማድረቂያ መደርደሪያ ቦታ ላይ ያስቀምጣል።
- ልጁ የወረቀት ኩባያውን ይጥላል።
- ልጆች ጥርሳቸውን ከቦረሹ በኋላ እጃቸውን ይታጠቡ።
- ገንዳውን በ 3-ደረጃ ሂደት ይጸዳል (ማጽዳት፣ ማለቅለቅ፣ ፀረ-ተባይ ማጥፊያን ተጠቅሞ ማጽዳት)።